# የስኬታማ ሕይወት ምክንያቶች

መንፈሳዊ ጉዞ የጀመሩ ሰዎች ሁሉ በስኬታማነት ከፍጻሜ አያደርሱትም። ይሄ የሚሆነው እግዚአብሔር ለአንዳንዶች የሚያዳላ ሌሎችን የማያግዝ ስለሆነ አይደለም። ምክንያቱ የትኛውም የሚጀምሩት የሥራ ዓይነት በቀላሉ ውጤታማ ስለማይሆንና የሚያስከፍለው ዋጋ ስላለ ነው። የጀመሩት የመንፈሳዊ ሕይወት ሥራም ሆነ ማጭበርበር የሌለባቸው የምድራዊ ኑሮ ሥራዎች ውጤታማ ለመሆን የሚጠይቁት ነገር በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው። እነዚህም፦

1. **ብርቱ ፍላጎት (ጥማት/መራብ)** (Strong desire, hunger and thurst for…) Mt 7:7-8፣ ኢሳ 44:3 ፡ -

ፍላጎት ሰውን ወደተለያየ ጎዳና የሚነዳ ኃይል ነው። ፍላጎት በሰው የሕይወት ዘመን ሁሉ አብሮ ይኖራል። ፍላጎትን ከግብ ለማድረስ እቅድ መንደፍና የአፈጻጸሙ ቅደም ተከተል በማውጣት ለሥራ የሚያስከፍለውን ዋጋ ለመክፈል ራስን ማዘጋጀት ነው። አንድን አላስፈላጊ ፍላጎት ለማስወገድ ብቸኛው መንገድ እርሱን የላቀ ጠቀሜታ በሚያስገኝ ፍላጎት/ከፍ ባሉ ዓላማዎችና ግቦች መተካት ነው። አንድ ሰው በብርቱ የፈልገውን ነገር ያገኘዋል። ምክንያቱም ያ የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት የሚጠይቀው መስዋእትነት/ዋጋ ከሚያገኘው ነገር ጋራ ሲያመዛዝነው የላቀ ዋጋ ሊከፍልበት የሚገባ መሆኑን አመዛዝኖ ስለሚያቀውና ለመክፈል ዝግጁ ሆኖ ስለሚተገብረው ነው።

ለስኬታማነት መነሳት ለዚያ ግብ ልብን ከማዘጋጀት ይጀምራል። እዝ 7:10፤ እዝራ ልቡን ያዘጋጀው ለ3 ተያያዥ ጉዳዮች ነበር። እነዚህም የእግዚአብሔርን ቃል/ፈቃድ ለማወቅ፣ ያወቀውን የአምላኩ ፈቃድ የሚያስከፍለውን ዋጋ በመክፈል ራሱ ሊተገብር እና ሌሎችን በማስተማር ለመለወጥ ነበር። በዚህ አካሄዱ እግዚአብሔርም ስለ ደገፈው እዝራ ሥራው ተከናወነለት።

ክርስቲያን በብርቱ ሊፈልጋቸው የሚገቡ የከበሩ ነገሮች፣ ግቦች/ዓላማዎች አሉ፦

**ሀ. እግዚአብሔር ራሱን መፈለግ፦** እግዚአብሔር ሰውንና ለሰው የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ የፈጠረ፣ የሰውን ሕይወትና ጎዳና ሊያቃና ከክፉም ሁሉ አጥር ሊሆን የሚችል አምላክ ስለሆነ ከሁሉ ነገር በቅድሚያ ሊፈለግ የተገባው ነው። ከእርሱ ያልሆነ ምንም በጎ ስጦታና በረከት የለም። ታማኝና በሁሉም ማንነቱ አስተማማኝ መመኪያ የሚሆን ስለሆነ የሚያሳርፍና እምነት የሚጣልበት አምላክ ነው። ሰው ማናቸውም በጎ በረከቶች ከመፈለጉ በፊት የሰው ሕልውናና የእነዚያ በረከቶች ሁሉ ምንጭ የሆነውን እግዚአብሔር በመፈለግ ከሁሉም በላይ በእርሱ ደስ በመሰኘት ከእርሱ ጋር ሕብረቱን/አካሄዱን ለማስተካከል አርሱን ደስ የሚያሰኘው ነገር በማድረግ፣ የሚጠላውን ነገር በማስወገድ፣መገኘቱን መፈለግ ይገባዋል። እግዚአብሔር ደግሞ ኤር 29፥13-14 ላይ “እናንተ ትፈልጉኛላችሁ፣ በፍጹም ልባችሁም ከፈለጋችሁኝ ታገኙኛላችሁ፤ …” ብሏል። (ኢሳ 55፥6፣1ዜና 28:9፣ አሞ 5፥6፣)

መዝ 105፡4 "ወደ እግዚአብሔርንና ወደ ኃይሉን ብርታት ተመልከቱ፤ ፊቱንም ዘወትር ፈልጉ" ሲል፦ ፊቱን መፈለግ ማለት ከእርሱ ጋር ያለ ሕብረት የሰመረ እንዲሆን መፈለግ፣ መስማማትን/የቅርብ ወዳጅነትን፣ የሚያደርጉት ነገር በእርሱ ፊት ተቀባይነት እንዲያገኝ መፈለግ፣ መገኘቱን መፈለግ ማለት ነው።

**ለ. የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን መፈለግ፦** የእግዚአብሔርን መንግሥት ክርስቶስ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ባለበት በላይ በሰማይ ያለውን ዘላለማዊው ክብርን፣ ሕይወትና የርስቱን ባለጠግነት ያለበት ነው። የክብርን ንጉስ ውበት ፊት ለፊት ማየት የሚቻልበት ነው፤ ይህን እንዲወርሱ በላይ ያለውን መሻት፣ መፈለግ ነው። (ማቴ 6፡33፣ ቆላ 3፡1-2፣ 2ቆሮ 5፡1-2፣) የእግዚአብሔር መንግሥት ከእግዚአብሔር የሚገኘው ጽድቅና ሰላም፣ በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታና ዕረፍት የሰፈነበት ነው (ሮሜ 14፡17፣ ኢሳ 14፡6-7።) ይሄ ሰማያዊና ዘላለማዊ ርስት ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ከሁሉም ነገር በላይ ሊፈልገው የሚገባ ነው። ሰው ዓለምን ሁሉ ከሚያተርፍ እግዚአብሔር በሰማይ ያዘጋጀውን ርስት መውረስ በብዙ እጥፍ ይበልጣልና።

ጽድቁን መፈለግ ማለት ደግሞ በማቴ 5፡3-12፣ የተዘረዘሩትና መሰል የጽድቅ ተግባራትን ማድረግ መፈለግ ነው። አማኝ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን የሚፈልግ ከሆነ እንዲሰጠው በጸሎት ሲጠይቅ ሌላው ምድራዊ ነገርም እንደሚጨመርለት የእግዚአብሔር ቃል ያስረዳል።

**ሐ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን መፈለግ**፤ 1ቆሮ 12፡31፣ 14፡1፣12፣ እነዚህ ስጦታዎችን የመፈለግ ምክንያቱ ጌታን በተሻለ ሁኔታ ተነቃቅቶ ለማገልገል፣ ነፍሳትን ለጌታ ለመማረክ፣ በልዩ ልዩ ቀንበርና እስራት ውስጥ ያሉት ሰዎች ነጻነት አግኝተው በጌታ አርፈው እንዲያከብሩትና እንዲያመሰግኑት እንዲሁም እውነተኛ ደቀመዛሙርት በማፍራት ለጌታ የተገባ ኑሮ እንዲኖሩ ለማብቃት ነው። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የተለያዩ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ስለሚሰጥ በተሰጡት ስጦታ ተግተው እያገለገሉ ተጨማሪ ስጦታዎችን እንዲሰጥ በጸሎት መጠየቅ ይቻላል።

2. **ጽኑ እምነት** (ቀጣይነት ያለው፣ አንዴ ከፍ አንዴ ዝቅ የማይል/ተለዋዋጭ ያልሆነ) 2ዜና 20፡20፣ ኢሳ 40፡31 እምነት በትክክል ከእግዚአብሔር ነው ብለው ለተቀበሉት እውነት ተግባራዊ ምላሽ ለመስጠት የሚንቀሳቀሱበት ጉልበት/አቅም ነው። እግዚአብሔር በተናገረው መንገድ ለመጓዝ ሲጀመር አንዳንድ ስጋቶች ሲኖሩ ጉዳዩን በእግዚአብሔር ፊት አኑሮ በእምነት ጉዞ መቀጠል ያሻል። መዝ 55፡22፣ 1ጴጥ 5፡7 እግዚአብሔር ሥሩት ያለው ስራ በሰው እይታ ምቹ የሚመስሉ ሁኔታዎች ኖሩም አልኖሩ ስለ እነርሱ ከማሰብ ይልቅ ከሁኔታዎች ሁሉ በላይ በሆነው ጌታ ሙሉ በሙሉ በመተማመን ያዘዘውን ማከናወን ነው። ሮሜ 4፡18-21፣ ምሳ 3፡5፣

   በእግዚአብሔር ታምነው ፈቃዱ በሆነ መንገድ በመራመድ ላይ እያሉ አንዳንድ ችግሮች ሊገጥሙን ይችላሉ። በዚህ ወቅት ከመረበሽ ወጥቶ እግዚአብሔር ለበጎ እንደሚለውጠው አምኖ ማመስገን ነው። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሳሉ እግዚአብሔር አንዳንድ ውጣ

ውረዶች እንዲያጋጥሙ የሚፈቅደው በፈታኙ ወቅት ለፈቃዱ ታማኝ ሆነው ሲጸኑ እግዚአብሔር ቀድሞ የተናገረውን የማዳኑ/የኃይሉ ታላቅነት እውን ሆኖ እንዲታይና ከበፊቱ ይልቅ በእርሱ ላይ ያለ እምነት እንዲያድግ ነው።

3. **እግዚአብሔርን ቃል/ፈቃድ መተግበር**; ዘዳ 7፡12-15፣ ኢያ 1፡7-9፣ ሚክ 6፡8፣ ማቴ 12፡48-50፣ ዮሐ 15፡14፣
   አሞ 5፥14 "በሕይወት ትኖሩ ዘንድ፣ መልካሙን እንጂ ክፉውን አትፈልጉ፤ ከዚያ በኋላ እንደ ተናገራችሁት፣ የሰራዊት አምላክ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሆናል።"

   ከዚህ በላይ የሰፈሩት ጥቅሶች እግዚአብሔር በቃሉና በመንፈሱ አማካይነት አድርጉት የሚላቸው ነገሮች ማድረግ፣ በሰውም ዘንድ ታላቅ አርአያነት ያለውና የእግዚአብሔር ወዳጅነትና ታማኝ አገልጋይነት ተገልጦ የሚታይበት፣ ከእግዚአብሔርም ዘንድ ታላቅ ወሮታ የሚያስገኝ ነው። አምላካችን ትዕዛዛቱን ተግተው የሚተገብሩትን ከአንዳች መልካም ነገር አያጎድልባቸውም።
   ከዚህ በታች የተጠቀሱት ዋና ዋና የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆኑ ነገሮች ሰፍረዋል።

***ሀ. የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች በማሰላሰል*** *ማመንና ያመኑትን ቃል በአፍ መናገር/ማወጅ፣ ኢያሱ 1፡8፤ መዝ 1፡1-3፤ 2ቆሮ 4፡13፤ ሮሜ 10፡8-10።*

*ማሰላሰል፣ መጽሐፍ ቅዱስን በቃል እያጠኑ በአእምሮ ማስታወስ/መሸምደድ ብቻ ሳይሆን ቃሉ ወደ መንፈሳችን ዘልቆ በመግባት እንዲሞላና እምነት እንዲፈጥር ያስችላል።*

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰራው በዙፋኑ ባለበት ወሰን አልባ ኃይሉ ሳይሆን በእያንዳችን ውስጥ ባስቀመጠው ኃይል ልክ ነው። ኤፌ 3፡20፣ ሐሥ 1፡4-8።

*መንፈስ ቅዱስ በእኛ ላይ በመጣ ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች አንዱ የሆነው ኃይል ተቀብለናል። የኃይሉ እምቅ በውስጣችን መኖሩ ብቻ በቂ አይደለም። ያን ኃይል ስራ ላይ ለማዋል አክቲቬት ማድረግ/ማነሳሳት ያስፈልጋል። ፊሊጵ 2፡13።*

እግዚአብሔር ቃሉን አሰላስሉ ያለበት ምክንያት በውስጣችን ያስቀመጠውን ኃይል ለማነሳሳትና አስተሳሰባችን ተለውጦ ሀሳባችን ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር እንዲስማማ፣ እንደ እግዚአብሔር አሳብ እንዲሆን ነው። ሁል ጊዜ በማንኛውም ሰልፍ ወይም ችግር ወቅት የአሸናፊነት አስተሳሰብና (አዎንታዊ አሰተሳሰብ) እምነት ይዘን አንዳንዴ ውጤታማ በሌላ ጊዜ ውጤት አልባ በመሆን ፈንታ በተከታታይነት ሁል ጊዜ ስኬታማና ድል አድራጊ እንድንሆን ነው።

*ማሰላሰል ማስተዋልን ይሰጣል፣ አእምሮንም ያድሳል። የእግዚአብሔርን ቃል/ፈቃድ ለማድረግ ያነሳሳል/ያነቃቃል/ ይገፋፋል። ይህም የሚሆነው አንድ ዓይነት ጉዳይ በገጠመን ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዚያ ጉዳያችን ጋር የሚገናኝ የተስፋ ቃል ፈልገን በማግኘት ያንን ቃሉ በማሰላሰል ሂደት መንፈስ ቅዱስ በዚያ ቃል ሬማ ስለሚሰጠን /ስለሚናገረን/ ነው፣ ይህም በተራው እምነትን ስለሚያስገኝ ነው። እግዚአብሔር የሰጠን ሬማ ወይም የምናሰላስለው*

የአግዚአብሔር የተስፋ ቃል በእምነት ስንናገረው መንፈስና ሕይወት ወይም ነገሮችን የሚለውጥ ኃይል ይወጣል፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ማሰላሰል ብቻ ሳይሆን ቃሉን ስናሰላስል የበራልን እውነት በመናገር/በማወጅ አማካይነት የሚወጣው ኃይል የተፈለገው ውጤት እንዲገኝ ለማድረግ ነው፡፡

**ለ. ላወቁት የእግዚአብሔር ታላቅ ማንነት ሙሉ በሙሉ በመገዛት** አድርጉት የሚለውን ሁሉ ተግባር ላይ ማዋል በመጀመር በዚያው ሳያቋርጡ ቀጥሎ በቅድሰና በመኖር ከእርሱ ጋር የሰመረ ኅብረትን/የቅርብ ወዳጅነት መመስረት ነው፡፡

**በፍቅር መኖር ፡-** ማቴ 22፡37-38፣ ከሁሉ በላይ አግዚአብሔርን መውደድና፣ ባልንጀራን እንደራስ መውደድን ይጨምራል፤ እግዚአብሐሔርን ከወደዱ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውን ሁሉ ማድረግ አይከብድም፡፡ ሰውን ሁሉ እንደራስ ከወደዱ ደግሞ ሁሉን ሰው በትህትናና በአክብሮት በመቅረብ አቅም በሚፈቅደው መጠን ለራስ እንዲደረግ የሚፈልጉትን ሁሉ ለሌሎች ማድረግ ያስችላል፡፡

1. ከዓለማዊ ምኞት ተለይቶ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ቃል መገዛትና በመንፈስ ቅዱስ መመራት፣ በሁሉም ነገር እግዚአብሔርን ማስቀደም ነው፡፡ ሮሜ 8፡5፣14
2. እግዚአአብሔርን መፈለግ እግዚአብሔር የሚወደውና የሚጠላውን/ፈቃዱን መንገዱን ስርአቱን ምን እንደሆነ ከቃሉ አጥንቶ በማወቅ መተግበርን ቀዳሚ አላማ አድርጎ ስለምድራዊ ኑሮ መስራት ሁለተኛ ተግባር ማድረግ ነው፡፡ እግዚአብሔርን የምንፈልገው ምድራዊ ነገር እንዲሰጠን ብለን ከሆነ ቀዳሚ ግባችን እግዚአብሔርን ማግኘት ሳይሆን ምድራዊ ነገር ነው ማለት ነው፡፡ ዮሐ 8፡29 የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናደርገው እርሱን ደስ ለማሰኘት ከመፈለግ የተነሳ ከሆነ እርሱም ምን እንደሚያስፈልገን ስለሚያውቀ ይሰጠናል፡፡
3. ባላመኑት ላይ መልካም ተጽዕኖ የሚያሳድር መልካም ተግባር ማከናወን (ፍቅር፤ ትህትና፣ ትእግስት፣ ይቅር ማለት፣ ቸርነት፣ ሰውን ሁሉ ማክበር …በማሳየት)፤

**ሐ. እንደ ፈቃዱ መጸለይ/ለሰው ሁሉ መማለድ፣** ሐሥ 6፡24

ሉቃ 6፥12፣ "ከእነዚያም ቀናት በአንዱ ኢየሱስ ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ፤ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ፡፡"

ሉቃ 18፥1 "ደቀ መዛሙርቱ ሳይታክቱ ሁል ጊዜ መጸለይ እንደሚገባቸው ለማሳየት ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤"…..

ሉቃ 21፥36 "ስለዚህ ከሚመጣው ሁሉ እንድ ታመልጡና በሰው ልጅ ፊት መቆም እንድትችሉ ሁል ጊዜ ተግታችሁ ጸልዩ፡፡"

ሮሜ 15፥30 "ወንድሞች ሆይ፤ ስለ እኔ ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ የተጋድሎዬ አጋር እንድትሆኑ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ፍቅር እለምናችኋለሁ፡፡"
ሐሥ 6፥4፣ "እኛ ግን በጸሎትና በቃሉ አገልግሎት እንተጋለን፡፡" (1ተሰ 5፡17፣ ሉቃ 18፡1፣)

እነዚህ በጸሎት ስለመትጋት የሚያመለክቱ ጥቅሶች መደዳ ያሰፈርኩበት ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ረዘም ያለ ጊዜ ወስዶ መጸለይ ጊዜን ማጥፋት ነው ብለው የሚያስተምሩ ስላሉ ነው፡፡ እነዚህ ከላይ የሰፈሩት ብቻ ሳይሆን በርካታ በጸሎት ስለ መትጋት የሚያስተምሩ ክፍሎች እያሉ እንዲህ ዓይነት ከቃሉ ጋር የማይስማማ ትምህርት መከተል እንደ ማይገባ ለማሳሰብ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስና ሐዋሪያቱ፣ ነቢዩ ዳንኤል ለ21 ቀናት፣ ነብይት ሐና ለአስርት ዓመታት ተግተው ከጾም ጋር ጸልየዋል፡፡ ሉቃ 2፡36-38፣

እግዚአብሔር ደግሞ ወደ እኔ ጩሁ፣ ለምኑ ይሰጣችኋል፣ ፈልጉ ታገኛላችሁ፣ አንኳኩ ይከፈትላችኋል፣ የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእኔ ላይ ጣሉት፣ በማለት ወደ እርሱ ለመቅረብ በኃጢአታችን ምክንያት መብት ያልነበረን ሰዎችን በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ራሱ የመቅረብና የመለመን ልዩ እድል ሰጥቶናል፡፡ እስቲ አስቡት፣ ማንኛውም የምድር ባለጠጋ ሰው ወይም ንጉስ፣ ጥቂት ሰዎች እንኳን በየእለቱ ፊቱ ቀርበው እንዲለምኑት የማይፈቅደውና የማይወደውን ነው ትልቁ እግዚአብሔር ልመናችንን መስማት የሚፈልገው፡፡

***መ. ለምድራዊ ኑሮ የመንፈሳዊውን ሥራ ሚዛን ሳያዛቡ በርትቶ መስራት፡-***

በቁሳዊ በረከት ራስን ለመቻልና ቤተሰበሰን በአግባቡ ለማስተዳደር ሰርቶ ማግኘት ያስፈልጋል፤

ኤፌ 4፡28፣ 1 ተሰ 4፡11-12፤ 2ተሰ 3፡7-14፣ መክ 2፡24፤ ሐሥ 20፡35፤ 1ቆሮ 4፡12፤ ባላመኑት/በውጭ ባሉት ሰዎች የእለት ተእለት አኗኗራችን ተቀባይነት/አክብሮት እንዲያገኝ (ወንጌል እንዳይናቅ) የማንኛውም ሰው ጥገኛ/ተደጋፊ ከመሆን ለመላቀቅ፤ የሚያስፈልገን ነገር በእጃችን እንዲኖርና ተግቶ በመስራት አግኝተን ለሚያስፈልጉን ነገሮች ማዋል ያስችላል፡፡

ለምድራዊ በረከት መስራት የሚገባው ራስንና ቤተሰብን በአግባቡ ለማስተዳደር የሚያስችል የኢኮኖሚ አቅም ከመፍጠር አልፎ በተለያየ ችግር ላሉት የሚያካፍሉት ነገር እንዲኖር፤ ለወንጌል ስራ ድጋፍ ለመስጠት፣ እንግዳ ለመቀበል፤ ስራፈቶች ላለመሆን በጽድቅ መንገድ ብቻ ለማግኘት መስራት አለብን፤ ለበጎ አድራጎት ስራም ለመብቃት ነው እንጂ ገንዘብን ከጌታ እኩል ወይም አብልጦ ለመውደድና በገንዘብ ወደ መመካት ለመድረስ መሆን የለበትም፡፡

በብሉይ ኪዳን ባለጠጋ የነበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ስም ተጠቅሶ እናያለን ምሳሌ አብርሐም፣ ኢዮብ፣ ዘዳ 28፡13፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚመላለስ ሰው ራስ እንጂ ጅራት፣ አበዳሪ እንጂ ተበዳሪ፣ ፊተኛ እንጂ ኋለኛ እንደማይሆን ተደንግጓል፤ ዘዳ 8፡18፤ 1ሳሙ 2፡7-8፣ መዝ 34፡10፣ 84፡11፤ ምሳ 10፡22፣

በአዲስ ኪዳንም ተለያዩ የቃሉ ክፍሎች የእግዚአብሔር ህዝብ የምድርም በረከት ባለቤት/ባላደራ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ 2ቆሮ 6፡10፤ 8፡9፤ ሮሜ 8፡32፤ 1ቆሮ 3፡21-22፤ ፊጵ 4፡19፤

ነገር ግን በዚህ ዓለም ገንዘብ የሰማይ ሀብት ማካማቻነት ለማዋል መገልገል እንጂ መመኪያ ወይም ለፉክክር/አኔ እበልጥ ውድድር ውስጥ ለመግባት መሆን እንደሌለበት ያዝዛል፡፡ ሉቃ 16፡ 9፤1ጢሞ 6፡17-18፣

**ሠ. እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ የፈጸመውን የማዳን ሥራና በጎነቱን በውጭ ላሉት መመስከር፤** ሮሜ 10፡9-10፣ 1ጴጥ 2፡9፣

በተሰጡ የጸጋ ስጦታዎች በጌታ ያመኑት በእግዚአብሔር ቤት እንዲጸኑ፣ በመንፈሳዊ ህይወታቸው እንዲያድጉና ያልዳኑትም ወደ አግዚአብሐር መንግስት እንዲጨመሩ መስራት። በጌታ ቤት ያሉት እንደፈቃዱ በመኖር የባሕርይ ለውጥ በማምጣት መልካም አርአያነት ያላቸው ሲሆኑ በውጭ ያሉት ብዙዎች ወደ ጌታ ይሳባሉ። ስለዚህ በዚህ አገልግሎት በዋናነት ጠንክሮ መስራት የሚገባው ያመኑት በኑሮቸው እንዲቀደሱ ማበረታታትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ገልጦ ማስተማር ነው። ስለሆነም ዋና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው የክርስቶስ ኢየሱስን ወንጌል በተገቢ አኗኗርና በቃል ላላመኑት መግለጥ እንጂ በፈውስና ተአምራት ማገልገል ላይ አይደለም።

4. **በትጋት/ጠንክሮ መስራት፡-** የሚሰሩትን ስራ ሁሉና፣ የሚሰጡትን አገልግሎት

ያለማቋረጥ በትጋት/ጠንክሮ በመስራት መከናወን አለበት። (diligence፣ hard work,) ምሳ 12፡ 24፣27; 13፡4፣10፡4፤ ሉቃ 13፡24፣ 2ተሰ 3፡13፣ 2ተሰ፡3፡10፤

ክርስቶስን የሚመስል ሕይወት በትጋት የሚመጣ እንጂ በቀላሉ የሚደረስበት አይደለም። ትጋት ጠንክረው ከሚሰሩት በላይ አብልጦ መስራትን ያመለክታል። ከተራ ሰው የሚጠበቀውን ያህል ብቻ ሰርቶ አለመርካትን ያመለክታል። የተለያዩ ችግሮች በማንም ሰው ላይ የሚደርሱ ናቸው። ከእነዚህ ችግሮች አብዛኞቹ ጊዜያዊ ቢሆኑም ትጋት ከሌለ ግን ቋሚ ችግር ሆነው ይቀራሉ። መታከትና ስንፍና ስኬትን ይዘርፋሉ።

መዝ 40፡5 አንድ ሰው በህይወቱ ከተቀበለው በረከት ይልቅ እግዚአብሔር ለእርሱ ያቀደው/በውስጡ ያስቀመጠው እምቅ ኃይል እጅግ ታላቅና ተገልጦ የማይጨረስ ነው። የትኛውም ሰው በውስጡ የተቀመጠውን እምቅ ብቃት አሟጦ ሳይጠቀም /ሳይገለጥ ዘመኑን ይጨርሳል። ሰው ለእግዚአብሔር ራሱን በቀደሰ/በተሸነፈ/ወደ እርሱ በተጠጋ ልክ እእግዚአብሔር ያቀደለትን እየወረሰ/እየተቀበለ ይሄዳል። 2ዜና 26፡5፣

5. **ጽናት/ቁርጠኝነት፡-** ዕብ 10፡36፣ ምሳ 24፡10፣ ገላ 6፡9-10፣ 2ቆሮ 11፡26-28፣ Firm commitment, resoluteness)

እየተጉበት ያለው ነገር ፈጥኖ ውጤት ባያስገኝም በእምነትና **በጽናት** (በትዕግስት) የተፈለገው መልካም ውጤት እስከሚገኝ መቀጠል:: የሚያስፈሩሩ/ስጋት የሚፈጥሩ ሁኔታዎች/ነገሮች በገጠሙ ሰዓት የእነርሱን ብዛት/ኃይል አይቶ ከራስ አቅም ጋር በማወዳደር ፈንታ ከአምላካችን ማንነት ጋር አወዳድረናቸው ተሸናፊዎች መሆናቸውን አምኖ መቆም/መረጋጋት/ደፍሮ መዋጋት።

በጣም የሚያሳምም ነገር በየሳምንቱ .... ሊከሰት እንደሚችል በማሰብ በጉዳዩ የበላይ ለመሆን (በሁሉም የሚደርስ እንደሆነ ለመቁጠር) ራስን ማዘጋጀት። አንድ ችግር ካለፈ በኋላ ሌላ ችግር አይደርስብኝም ብሎ አለመዘናጋት። ማቴ 6፡34፣ ኢሳ 32፡8፣ ዳን 11፡31-32፣ 12፡13

6. እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነ ምክር በመፈለግ/መጠየቅ/ጠቢባንን ማማከር፡- ያለው እውቀትና ዕቅድ አሰራርና ጥራትም በየጊዜው እየፈተሹ በማሻሻል መቀጠል። ምሳ 11:14፣ 15:22፣ 24:6፣ መክ 10:10፣ ምሳ 16:1፣19:2 ምሳ 24:3-6፣

እግዚአብሔር ለሁሉም አማኝ ኢየሱስ ክርስቶስን፣ መንፈስ ቅዱስን፣ የጸጋ ስጦታዎችን፣ ህያው ቃሉን… ሰጥቶናል። በሁሉም ሰው የህይወት ጉዞ ወጣ ገባዎችና ጠመዝማዛዎች አሉ። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ስጦታዎች ተሰጡን ማለት የተትረፈረፈ ድል አድራጊነት መድረስ የሚያስችለን ስጦታዎች አሉን ማለት ነው። ሰው በዚህ ቃል እምነት ካለው በምንም ሊሸነፍ አይችልም።

ለሽንፈታችን ዋናው ምክንያት እና ወሳኝ ነገር የደረሰብን ፈተና ዓይነትና ጥንካሬ ሳይሆን የምንሰጠው አጸፋዊ ምላሽ ተገቢ አለመሆን ነው። በሰዎች ህይወት ላይ ልዩነት የሚያመጣው እነዚህን መርሆዎች የመተግበር ያለመተግበር ጉዳይ ነው። በእግዚአብሔር ቁጥጥር ስር ስንሆን ነገሮች ሁሉ በቁጥጥራችን ስር ይሆናሉ። በእግዚአብሔር ቁጥጥር ስር ካልተኮነ በአእምሮ ውጥረት፣ በተስፋ መቁረጥ፣ በፈተና፣ በፍጥረታት ውጊያ …. በእግዚአብሔር የተዘጋጀልን በረከት ሳንወርስ/ ስኬታማ እንዳንሆን ሊያደርግ ይችላል። ያዕ 4:7፣ ሉቃ 10:19፤

ሊሰሩት ያሰቡት ሥራ ከመጀመር በፊትና ከጀመሩም በኋላ በየጊዜው የመንፈስ ቅዱስን ምሪት መጠየቅና የሰጠውን ምሪት ተከትሎ መስራት ተገቢ ነው። ሊጀምሩት ያሰቡት ሥራ መንፈሳዊ ሥራ ካልሆነ በዚያ ሙያ ልምድ ያዳበሩና ከፍ ያለ ሥልጠና የወሰዱ ባሙያዎችን አፈላልጎ ማማከር እንዲሁ በግምት ከመራመድ በጣም የተሻለ ነው።

በጉልበት ጠንክሮ መስራት ጥሩ ነው። ነገር ግን በአእምሮ የላቀ እውቀት ተጠቅሞ ሥራን ቀላል በሚያደርግ ዘዴ መስራት ውጤቱ ከጉልበት ስራ በጣም የተሻለ ነው። 2.5 በመቶ የአሜሪካ ዜጎች ብቻ ገበሬዎች ቢሆኑም የአገራቸው ህዝብ ፍላጎት ከማርካታቸውም በላይ ለዓለም ገበያ ትልቅ መጠን ያለው ምርት ያቀርባሉ። ይሄ የሚሆነው በቴክኖሎጂ ውጤቶች ስለሚጠቀሙ ነው። የኢትዮጵያ ከ80 በመቶ በላይ የሆነው ሕዝብ አርሶ አደር ቢሆንም የአገሪቱን የምግብ ፍላጎት ማርካት አልቻለም። ከዚህም የላቀው ጥበብ ደግሞ ለእግዚአብሔር ቃል በመገዛት መኖር ነው። መክ 10:10፣ ዘዳ 4:6፣ ምሳ 4:2

ባርኮት በወጣትነትና በጉልምስና እድሜ ብቻ ሳይሆን እድሜ ከገፋ በኋላም እንደሚቀጥል መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጣል። መዝ 92:12-14፣ ጻድቃን እንደ ዘንባባ ይንሰራፋፋሉ፣ …. ባረጁ ጊዜ እንኳ ያፈራሉ፣ እንደ ለመለሙና እንደ ጠነከሩ ይኖራሉ። ስለዚህ በመንግሥትም ሆነ በግል ድርጅት ተቀጥረው ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ ጡረታ ቢወጡም በዕድሜ መግፋት ተስፋ ሳይቆርጡ የሚችሉትን ያህል ሥራ ቢያከናውኑ ራሳቸውንና ሌሎችን የሚጠቅሙ ይሆናሉ።